**የዩኤስ ፍትህ ድፓርትመንት**

የሲቪል መብቶች ክፍል

---

*ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ህግ*
*950 Pennsylvania Ave, NW - RFK*
*Washington, DC 20530*

## የሲቪል መብቶች ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ኤሪክ ኤስ. ድሬባንድ (Eric S. Dreiband) መግለጫ
## ለኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019 (COVID-19) ምላሽ ሲሰጥ የሲቪል መብቶችን መጠበቅ

ኮሮናቫይረስ በሽታ 2019 (COVID-19) አስመልክቶ፣ የህዝብ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ ሲታይ፣ የዩናይትድ ስቴትስ የፍትህ ዲፓርትመንት የሲቪል መብቶች ክፍል የህገ-ወጥ መድልዎ ሰለባዎች የሲቪል መብቶች ሲጣሱ የት መሄድ እንዳለባቸው ማወቃቸውን ለማረጋገጥ ይህንን መግለጫ አውጥቷል። .

በዘር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በአካለ ስንኩልነት እና በሌሎች የተጠበቁ ምድቦች ላይ የተመሠረተ አድልዎ በበርካታ የፌዴራል ሕጎች የተከለከለ ሲሆን የወንጀል ወይም የፍትሐ ብሔር ተጠያቂነትን ያስከትላል። ምሳሌ፣ ይመልከቱ https://www.justice.gov/crt/page/file/921291/download። በተጨማሪም በእነዚህ እና በሌሎች በተጠበቁ ምድቦች ላይ የተመሠረተ የጥላቻ ድርጊቶች የፌዴራል የጥላቻ ህጎችን ይጥሳሉ። ምሳሌ፣ ይመልከቱ፣ https://www.justice.gov/crt/hate-crime-laws። አድልዎ በተለያዩ የአገባቦች፣ በትምህርት፣ በስራ፣ በጤና እና በደህንነት፣ በመኖሪያ እና የሕዝባዊ ቅበላ ቦታዎችን ጨምሮ በብዙ የተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ሊፈጠር ይችላል።

ለ COVID-19 ወረርሽኝ ዓለም አቀፍ ምላሽ በቀጠለበት ሁነታ መምሪያው የሲቪል መብቶች ህጎችን ለማስፈፀም በንቃት ይቀጥላል። ፍርሃት እና ጭፍን ጥላቻ በዘር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በአካለ ስንኩልነት፣ ወይም በሌሎች በተጠበቁ ክፍሎች፣ ከሌሎች ነገሮች በዘለለ፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ጥቅማ ጥቅሞችን፣ አገልግሎቶችን፣ ስራዎችን እና መረጃዎችን ከመጠቀም አለመገደባቸውን ማረጋገጥ አለብን። በተጨማሪም ትክክለኛ የድንገተኛ ሁኔታ እና የጤና መረጃ ተደራሽነት ሁሉም ሰዎች በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ የማድረግ እና እራሳቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውን እና ማህበረሰቡን በአጠቃላይ የመጠበቅ ችሎታን ለመስጠት ወሳኝ ነው።

**በተጠበቁ ምድቦች ላይ የጥቃት እርምጃዎችን ወይም ማስፈራራቶችን ጨምሮ ህገ-ወጥ የሆነ አድልዎን ለማስወገድ ሁላችንም አንድ ሆነን መሥራት በጣም አስፈላጊ ነው።** እንደማንኛውም የድንገተኛ አደጋዎች፣ የ COVID-19 ወረርሽኝ በብዙ የተለያዩ ዘሮች፣ ሀይማኖቶች እና ብሔሮችን እንዲሁም የአካል ጉዳተኞች ላይ ጫና አሳርፏል። ህገ-ወጥ መድልዎ ሰዎች መረጃ ለማግኘት እና ለመታከም እንዲመጡ ላያበረታታቸው ይችላል። **ህገ-ወጥ የሆነ አድልዎ ባህሪን የሚከለክሉ ህጎች በከባድ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ።**

**በዘር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በአካለ ስንኩልነት፣ ወይም በሌሎች በተጠበቁ ምድቦች ላይ በመመርኮዝ የመድልዎ ሰለባ ነኝ ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ቅሬታዎን እንዴት ማስገባት እንደሚችሉ በ** https://www.justice.gov/crt/how-file-complaint **እና በ** https://www.justice.gov/crt/fcs **መረጃ ማግኘት ይችላሉ። ከቅጥር ጋር በተያያዘ መድልዎ ዙርያ ቅሬታዎችን ወደ EEOC በ** https://www.eeoc.gov/employees/charge.cfm **አማካኝነት ማቅረብ ይችላሉ።** በተጨማሪም **የሲቪል መብቶች ክፍልን በ 855-856-1247 ወይም 202-514-3827 ነጻ የስልክ መስመሮቻቸው ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪ፣ ክፍሉ መረጃዎችን በ** https://www.ada.gov **(ከአካል ጉዳት ጋር የተያያዙ ርዕሶች) እንዲሁም** https://www.lep.gov **(የቋንቋ ትርጉም ተደራሽነት መረጃ) ያቀርባል።**

**በዘር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በአካለ ስንኩልነት፣ ወይም በሌላ በተጠበቀ ወገን ላይ የሚከሰቱ የኃይል ድርጊቶች ወይም ማስፈራራቶች በተመለከተ መረጃ ካለዎት እባክዎን በአከባቢዎ የሚገኘውን የ FBI ፊልድ አፊሰር ያነጋግሩ። የፊልድ አፊሰሮችን ዝርዝር በ** https://www.fbi.gov/contact-us/field-offices**ማግኘት ይችላሉ።**

የዩናይትድ ስቴትስ የፍትህ መምሪያ የሲቪል መብቶች ክፍል፣ በበመላው ፌዴራል መንግስት ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ድርጅቶች ጋር በመሆን፣ ከ COVID-19 ጋር የተዛመዱ የሲቪል መብቶች ጉዳዮችን መከታተሉን ይቀጥላል። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎንwww.justice.gov/crt/fcs ይመልከቱ። የፌደራል መንግስት ለ COVID-19 የሰጠውን ምላሽ

የሚመለከት የበለጠ መረጃ በ The White Houseይገኛል፡ የኮሮና ቫይረስ መመሪያዎች ለአሜሪካእናwww.coronavirus.gov።

*የመመሪያ ሰነዶች በሕግ በግልጽ ካልተፈቀደ ወይም በግልጽ በውል፣ ፈቃድ ወይም የትብብር ስምምነት ውስጥ ካልተካተተ በስተቀር፣ የመመሪያ ሰነዶች አስገዳጅ አይሆኑም እንዲሁም የሕግ ኃይል እና ውጤት አይኖራቸውም። ከአዋጅ 13891 እና ከአስተዳደር እና የበጀት ጽ/ቤት (Office of Management and Budget) አፈጻጸም ማስታወሻ ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ ዲፓርትመንቱ በዲፓርትመንቱ መመሪያ ፖርታል ወይም ሌሎች የስራ አስፈፃሚ ቅርንጫፎች እና ኤጀንሲዎች በሚገለገሉባቸው ተመሳሳይ የመመሪያ ፖርታሎች በኩል፣ ታሪካዊ እውነታዎችን ለማገናዘብ ካልሆነ በስተቀር፣ የማይደረስ ማንኛውም የመመሪያ ሰነድን አይመለከትም፣ አይጠቀምም፣ ወይም አይተማመንም። የትኛውም የመመሪያ ሰነድ የበጎ ፈቃደኝነት መመዘኛዎችን እስካስቀመጠ ድረስ (ለምሳሌ፣ የሚመከሩ ልምዶች)፣ እነዚያን መመዘኛዎች ማክበር በፈቃደኝነት ነው፣ እናም አለመታዘዝ የማስፈፀም እርምጃን አያስከትልም። የመመሪያ ሰነዶች ከሚመለከታቸው ህጎች ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ በዲፓርትመንቱ ሙሉበሙሉ ነጻ ውሳኔ ሊነሱ ወይም ሊቀየሩ ይችላሉ።*